## መመሪያ ቁጥር 1032/2017
## የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር 1032/2017

የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ጥሬ ጨው በሚመረትበት አካባቢ ብቻ እንዲሠሩ መደረጉ የንግድ ውድድርን የሚገድብ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለናፍታሊን ግዢ የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎችን ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርግና በግብይቱ ላይ ችግር የሚፈጥር ሆኖ በመገኘቱ፤

በጨው ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ነጋዴዎች ምርቱን አላግባብ በማከማቸት በገበያ ውስጥ ሰው ሰራሽ እጥረት እንዳይፈጥሩ መከላከል በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በሥራ ላይ ያለውን የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015 ለማሻሻል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ22 (1) (ለ) እና19(4) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 1032/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ማሻሻያ

የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ(3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፦

"3. "የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካ" ማለት በሀገሪቱ በማንኛውም ስፍራ የሚገኝ ሆኖ፦

ሀ) ጥሬ ጨውን በማጠብ እና በአዮዲን በማበልጸግ አዮዲን ያለበት መሆኑን በሚገልጽ እስከ 50 ኪሎ ግራም በሚይዝ ማሸጊያ በቀጥታ ለሰው ምግብነት ወይም ለምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች በጅምላ የሚያቀርብ፤ ወይም

ለ) ጥሬ ጨውን በማጠብ ጨዉ የታጠበ እና አዮዲን የሌለው መሆኑን በሚገልጽ እስከ 50 ኪሎ ግራም በሚይዝ ማሸጊያ በግብዓትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በጅምላ የሚያቀርብ፤ ወይም

(ሐ) ከውጪ ሀገር የሚገባውን የሚተካ ወይም ለውጪ ገበያ የሚውል የገበታ ጨው የሚያቀርብ ነው፤”

2. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተተክቷል፡-

“5. “ጅምላ አከፋፋይ” ማለት የጨው ምርትን ከጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች በመግዛት ለአነስተኛ የጨው አቀነባባሪዎች ወይም ለቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ነጋዴ ነው፤”

3. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (10) ተሰርዞ ንዑስ አንቀጽ (11) ንዑስ አንቀጽ (10) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

“10. “የምግብ ኢንዱስትሪ ግብዓት ጨው” ማለት በአዮዲን የበለጸገ ሆኖ ጨውን እንደ ግብአት ለሚጠቀሙ የምግብ አምራች ፋብሪካዎች የሚቀርብ ጨው ነው፤”

4. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (12) ንዑስ አንቀጽ (11) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

“11. “የኢንዱስትሪ ግብዓት ጨው” ማለት ያልታጠበ እና አዮዲን የሌለው ሆኖ ለምግብነት የማይውሉ ምርቶችን ለማምረት የሚያገለግል ለምግብነት የማይውል መሆኑን በሚገልጽ ማሸጊያ የሚቀርብ ጨው ነው፤”

5. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (13) ንዑስ አንቀጽ (12) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

“12. “የጨው ምርት መግለጫ” ማለት ሌሎች ዝርዝር መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የታጠበ፣ በአዮዲን የበለጸገ ወይም ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውል ጨው ስለመሆኑ በማሸጊያው ላይ የሚጻፍ መግለጫ ነው፤”

6. የመመሪያው አንቀጽ 2 ከንዑስ አንቀጽ (14) እስከ ንዑስ አንቀጽ (19) የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (13) እስከ ንዑስ አንቀጽ (18) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

7. በአንቀጽ 4 ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (8) ተጨምሮ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ (8) ንዑስ አንቀጽ (9) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡-

“8. ዘመናዊ የጨው ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፤”

8. አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፦

“3. ከማምረቻ ቦታ የሚወጣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል ያልታጠበም ሆነ የታጠበ ጨው ለምግብነት እንደማይውል በሚገልጽ ማሸጊያ እየታሸገ መውጣቱን ይቆጣጠራል፡፡”

9. የመመሪያው አንቀጽ 7 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፦

“ 7. የጥሬ ጨው አምራች ግዴታ

ጥሬ ጨው አምራች ጥሬ ጨውን በወቅቱ እና በጥራት በማምረት የገበያ ትስስር ለተፈጠረላቸው የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች እና ለምግብነት የማይውል መሆኑን በሚገልጽ ማሸጊያ አሽጎ በግብዓትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በጅምላ ያቀርባል፡፡”

10. አንቀጽ 8 እና አንቀጽ 9 ተሰርዘው ከአንቀጽ 10 እስከ 19 የነበሩት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 8 እስከ አንቀጽ 17 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

11. አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) የነበረው አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

“3. በጅምላ አከፋፋዮች አማካይነት ለምግብ ኢንዱስትሪዎች እና ለአነስተኛ የጨው አቀነባባሪዎች በአዮዲን የበለጸገ ጨው በማሸግ ለገበያ ያቀርባል፤”

12. አንቀጽ 8 ሆኖ የተሸጋሸገው አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (7) ተሰርዟል፡፡

13. አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (3) አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (3) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

“3. በገበያ ውስጥ የጨው እጥረት እንዳያጋጥምና የተረጋጋ የጨው ግብይት እንዲኖር አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡፡”

## 3. <u>*መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ*</u>

*ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በሚንስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡*

**አዲስ አበባ ህዳር 24 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)**

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር**